በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 7


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ግንቦት ፳፫ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

- ዛሬ በጣም ወሳኝ የሆነና ጥልቅ መንፈሳዊ መረዳትን የሚሻ አንድ ትምህርት እንማራለን፡፡
- እርሱም መንፈሳዊ ሕይወትንና የሰውነት ፈቃድን መፈጸም የተመለከተ ነው፡፡
- በጋብቻ  ሕይወት መንፈሳዊነትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም ምን ዓይነት ተዛምዶ አላቸው?
- የሰውነት ፈቃድን መፈጸም አስመልክቶ ያለው የእግአብሔር እቅድና ግብ ምን እንደሆነም እንማራለን፡፡
- በትዳር ሕይወት ስላለ የፈቃድ አፈጻጸም፣ መሰናክሎች፣ መንፈሳዊነትና የሰውነትን ፈቃድን በአግባቡ መፈጸምን የሚደግፉ ነጥቦችንም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንመለከታለን፡፡
- በተቀደሰው ትዳራችን የሚኖር መንፈስቀዱስ፣ የተስተካከለው መንፈሳዊ የሕይወት ደረጃችንና በትዳር ሕይወት ፈቃድን መፈጸም ስምምነት አላቸው፡፡
- በተቀደሰ ጋብቻ የምንኖር ከሆንን በክርስቲያናዊ ጋብቻ በተፈቀደልን የሰውነት ፈቃድን የመፈጸም ሕይወት ታላቅ ደስታን ማግኘት እንችላለን፡፡

## 1. የእግዚአብሔር እቅድ

- እግዚአብሔር ለትዳር ሕይወት ያለውን እቅድ አስመልክቶ ሦስት ነጥቦችን እንመለከታልን፡፡

### 1. ዘፍጥረት 1፡26-28፡፡

- ‹‹እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ፡፡ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡ እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡፡››

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

- ይህ የእግዚአብሔር እቅድ የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡
- እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር በጋብቻችን ስለሚኖር መንፈሳዊ የሆነ የሰውነትን ፈቃድ የመፈጸም ሕይወት አስተምሮናል፡፡ ይህንንም … ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት… በማለት ገልጦታል፡፡ -- ይህም ለሰው ዘር ሁሉ ጋብቻን አስመልክቶ የተሰጠ የመጀመሪያ ሕግ ነው፡፡
- እግዚአብሔር ለሰው ዘር ያዘጋጀው እቅድ መብዛት ነው፡፡ ይህንም ለአዳምና ለሔዋን ነግሮአቸዋል፡፡ አባቶቻችን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ ቅዱስ ቀሌምንጦስ እንደነገሩን ጋብቻቸውን በኤድን ገነት በቀደሰው ጊዜ አብሮአቸው በመሆን አረጋግጦላቸዋል፡፡ ***ዘፍጥ 2፡24፡፡***
- በኤድን ገነት ጋብቻን የመሠረተ እግዚአብሔር በገሊላ ቃና መልሶ በመባረክ ያረጋገጠው መሆኑን አባቶቻችን ነግረውናል፡፡

## 2. ***ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡፡***

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ « ተጠንቀቁ ! ተቀድሶ የተጀመረ ጋብቻ ንጹሕ፣ ቅዱስ ፣የተመረጠ፣ ምስጢር፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ በፊቱም የከበረ መሆኑን እወቁ!» በማለት አስጠንቅቆናል፡፡
- በመጀመሪያዎቹ አምስት ምዕተ ዓመታት የተቀደሰውን ጋብቻና ተራክቦንም የሚያራክሱ በርካታ የክህደት ትምህርቶች ይሰራጩ ነበር፡፡ በመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጉባኤ ሳይቀር ያገቡ ቀሳውስት እንዳይቀድሱ ለማድረግ ከመሞከር አንስቶ ብዙ የተሳሳቱ የክህደት ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ይህ ጋብቻን አራክሶ የሚመለከት አመለካከት በዘመኑ በነበሩ አባቶቻችን ውድቅ ተደርጎ ነበር፡፡
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በትምህርቱ የመራን ቀዳ ቆሮ 7፡3-5ን ወደ መመልከት ነበር፡፡

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

*3. ቀዳ ቆሮንቶስ 7:3-5::*

- ‹‹ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ:: ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ:: ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ::»
- ይህ ክፍል ቁጥር 3 በመጀመሪያ በትዳር ሕይወት ውስጥ ያለውን መፈላለግ (የሰውነት ፍላጎት) የሚመለከት ነው፡፡ ቀጥሎም ቁጥር 4 ተራክቦን አስመልክቶ እያንዳንዳችን በሰውነታችን ላይ ያለንን ሥልጣን የሚያስረዳ ሲሆን ቁጥር 5 ደግሞ ተራክቦን አስመልክቶ እንዴት ራሳችንን ሥርዓት ማስያዝ እንዳለብን ያስረዳል፡፡ *ተራክቦ* ማለት በትዳር ሕይወት የሰውነት ፈቃድን መፈጸም ማለት ነው፡፡
- መስማማት ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ያህል ጊዜ? ሰይጣን በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀምበት የሚችልበት ቀዳዳ አይኖረውም ይሆን? ሥርዓት እንዲኖረን ማድረግ ታላቁ መፍትሔ ነው፡፡
- ይህ መልእክት የያዘው በዛሬው ትምህርታችን የምንዳስሰውን ዋና ዋና ነጥቦች ነው፡፡
- ስለ መፈላለግ ወይም ስሜት ሲናገር መልዕክቱን የጀመረው … ባል ለሚስቱ የሚያስፈልጋትን ያድርግላት በማለት… ባልን በመምከር ነው፡፡ በተራክቦ ሴት ይህንን ናት፡፡
- ባሎች ሆይ ለሚስቶቻችሁ የሚገባውን አድርጉ፣ ደስ አሰኙአቸው፣ እንዲረኩ አድርጉአቸው ነው የተባለው፡፡

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

3. *ቀዳ ቆሮንቶስ 7፡3-5፡...*

- እንዲሁ ሚስቶችም ለባሎቻቸው የሚገባውን ያድርጉላቸው አለ፡፡
- ማንኛውም ሰው ከስሜትና በመፈላለግ የከሚኖረው ደረጃ ዘሎ ወደ አካላዊ ንክኪ ሊሄድ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች እንጂ እንስሳት አይደለንምና፡፡ ሰዎችም ብቻ ሳንሆን መንፈሳውያን ሰዎች ነንና፡፡
- ስለምን በባል ጀመረ? ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ባል የሚመለከተውን ይህን ጉዳይ ይረሳልና ነው፡፡
- ባል ሲሰጥ ሚስትም ደስ ተሰኝታ ትሰጣለች፡፡ ሁለቱም ክርስቶስ በቀደሰው ጋብቻ በተከበረው መኝታቸው በሰጣቸው በዚህ የተራክቦ ስጦታ ደስ ይሰኛሉ፡፡ ይህ የደስታ እንጂ የመሸማቀቅ ምንጭ አይደለም፡፡
- ‹‹ መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን ›› *ዕብ 13፡4፡፡*
- ወደ ቁጥር 4 ስንተላለፍ በተቀደሰው ጋብቻ ወደ ተከበረው መኝታችን ከመሄዳችን በፊት አልጋውን በትእምርተ መስቀል ምልክት እንባርከው፡፡ በመቀጠልም እግዚአብሔር ይባርከን ዘንድ አብረን ተያይዘን አባታችን ሆይ... ብለን እንጸልይ፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔርን ስላደረገልን ሁሉ እናመስግነው፡፡
- ቁጥር 4 የሚጀምረው ... ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤... በማለት በሚስት ነው፡፡ ምክንያቱም ለአንዳንድ ሴቶች አካላዊ ጉዳይ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባቸዋልና ነው፡፡ ስለዚህ ሚስቶችን ተው ለማለት በእነርሱ ጀመረ፡፡ ... እንዲሁ ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ፡፡ በማለትም ሥልጣኑ የጋራ እንደሆነ አስተማረን፡፡
- እውነተኛው የሰውነታችን ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡
- በትዳር ባለ ተራክቦ ከቅድስና ወደ ቅድስና እንገባለን፡፡ የመጀመሪያው የትዳሩ መቀደስ ሲሆን ሁለተኛው በተቀደሰው ተረክቦ የሚገኘው ነው፡፡ ማንኛውም ነገራችን ንጹሕ ከሆነ ተራክቦው የበለጠ ቅዱስ ነው፡፡

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

3. *ቀዳ ቆሮንቶስ 7፡3-5፡…*

- ይህም ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆኑ ዘንድ የሚያደርጉት ቀጥተኛ ግኑኝነት ነው፡፡ ሁለት ግማሽ ውሃ የያዙ ብርጭቆዎችን ውሃውን ከአንዱ ወደ አንዱ ስንገለብጥ እንደሚዋሐዱ አንድ ስለሆኑ፣ በየግላችን አይሆንም ለማለት ምንም ሥልጣን የለንም፡፡
- አሳዛኙ ነገር ግን ከሚስቶች ይልቅ ከዚህ በፊት በዚህ የማይወቀሱት ባሎች አይሆንም ባይ ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ ዛሬ ዛሬ ምን እየሆነ እንደሆነ ማወቅ እየቸገረ ነው፡፡ ምንም ይሁን ምን ሥልጣኑ የጋራ ነው፡፡
- ከሁለት አንዳቸው ታመው አንዳቸው ስለሌላው ሕመሙ ተሰምቶአቸው አይሆንም ይሉ እንደሆነ ነው እንጂ በባዶ ሜዳ በየግል አይሆንም ለማለት ለማንም አልተፈቀደም፡፡
- ቁትር 5 እንዴት ሥርዓት እንደምናሲዘው … ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ … በማለት ያስረዳናል፡፡
- ለተወሰነ ጊዜ ለጸሎትም ይሁን ጊዜውን ለመንፈሳዊ ነገር ለመጠቀም ተነጋግረን ሌላው ወገን ተስማምቶ የንስሐ አባትን ምክር ተቀብሎ አብሮ ለመጸለይ ለመጾም ካልሆነ በቀር በግል ተነስቶ ማድረግ አልተፈቀደም፡፡
- በመጨረሻ መንኩሶ ተራክቦን ትቶ ለመኖር እንኳ ለመወሰን ስምምነት ያስፈልጋል፡፡
- ጾሙን ወይም ጸሎቱን ጀምረን በመካከሉ አንዳችሁ መፈተን ቢገጥም እርስ በርሳችሁ ተጋገዙ፡፡ ይህ ምንም ስህተት የለውም፡፡ ካልተቻላችሁ ተስማምታችሁ የተቻላችሁን አድርጉ፡፡
- ከቅዱስ ቁርባን በፊት ለተወሰኑ ሰዓታት ስንጦም ዓይን፣ አእምሮአችን፣ ልባችን፣ ሆዳችን፣ ሰውነታችን ሁሉ መጾም አለበት፡፡ ምግቡ ንጹሕ ቢሆንም ከምግቡ ለተወሰነ ሰዓት እንጦማለን፡፡ ከተራክቦም ተስማምቶ እንዲሁ ሊሆን ይገባል፡፡

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

## *2. የእግዚአብሔር ግቦች*

I. አንድ መሆን

- ‹‹ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡›› *ማቴ 19፡2-3፡፡*

II. መብዛት (ዘር መተካት)

- ይህ አንድነት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምሕሮ ቢወልዱም ባይወልዱም ሳይለያዩ ለመኖር ነው፡፡
- በአንዳንድ የእምነት ድርጅቶች አንድነት ለመውለድ ነው፤ ካልወለደች/ደ ይለያያሉ፡፡

III. ደስ መሰኘት (በተራክቦና በመረዳዳት)

- እግዚአብሔር ይህን ግኑኝነት አስደሳች እንዲሆን አዘጋጅቶታል፡፡
- እግዚአብሔር በሰጠን በዚህ የተቀደሰ ስጦታ ሁሉ ደስ መሰኘት አለብን፡፡
- ‹‹ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር…» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈልን፡፡ *ቀዳ ጢሞ 6፡19፡፡*
- እግዚአብሔር ያለበት ነገር ሁሉ አስደሳች ነው፡፡ ያለ ፍርሃት በግኑኝነታች ተደስተን እግዚአብሔርን አንተ በመካከላችን በመኖርህ ደስ ተሰኝተናል ብለን እናመስግነው፡፡
- ለወንዱም ለሴትም የፈጠረው የተራክቦ አካላት የተፈጠሩት ለደስታና ዘር ለመተካት ምክንያት እንዲሆነን ነው፡፡

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

## 3. ተራክቦ

- እግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጀለት ይህ አካል አራት ደረጃዎች አሉት፡፡ ሴቶች በተራክቦ ጊዜ አራቱን ደረጃዎች ለማለፍ ረጅም ጊዜ ይወስድባቸዋል፡፡
- ሚስት ወደ ተራክቦ ከማለፍዋ በፊት በባልዋ ዘንድ ቁጥር አንድ ተመራጭ መሆንዋን ልብዋ ማረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ በመቀጠል፣ በሰውነት ወደ መነካካት፣ ተራክቦ ወደማድረግ እያሉ የእፎይታ አየር እስከሚተነፍሱበት ተራራ መውጣት ይሻሉ፡፡
- ባሎች ግን በፓራሹት ከአየር እንደተወረወረ ሰው ወርደው የሚፈልጉበት ቦታ ማረፍና የእፎይታ ትንፋሻቸውንም ወዲያው መጨረስ ይችላሉና ከሚችሉ ይልቅ መጠባበቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- ለተራክቦ የሚሆነው አካላችን የሚገኘው በመካከል ነው፡፡ በእግር መካከል አይደለም፡፡ ይህ በመካከል ያለ ሰውነታችን ከተቀደሰ መላው ሰውነታችንም የተቀደሰ ይሆናል፡፡
- ተራክቦ፡-
    - ጊዜ መስጠትን
    - ርኅራኄ መፈላለግ፣ በጎ ስሜት፣… ያለበት ፍቅርን
    - እርስ በርስ መናበብንና
    - ዋናውን ግብ አለመርሳትን ይሻል፡፡ ግቦቹም ከላይ በቁጥር ሁለት የተጠቀሱት ናቸው፡፡

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

## 4. የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች

- ሰይጣን ያገቡትንም ያላገቡትንም የሚዋጋው ቅድስናቸውን በመገናኛ ዘዴዎች፣ ልቅ የሆነ የወሲብ ፊልም በሚተላለፍባቸው መንገዶች ወይም ይህን በሚመስሉ መጻሕፍት፣ በኢንተርኔት፣ በቪዲዮ ፊልሞች፣... ነው።
- ከላይ ለተጠቀሱት ነገሮች መንገድ ያለን ጤናማ ያልሆነ አትኩሮት አእምሮአችንን ብቻ ሳይሆን ትዳራችንንም ሆነ ሕይወታችንን ሁሉ ያቆሽሸዋል።
- ይህ ተጽእኖ መላ ማንነታችንን ከሰው ጋር ያለንን ግኑኝነት ሳይቀር ያበላሻል።
- ልቅ የሆነ የወሲብ ፊልም በሚተላለፍባቸው መንገዶች (Pornography) የተጠመዱ ሰዎች የሚመለከቱት የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ ነው። ከትዳር አጋራቸውም ጋር ፈቃዳቸውን ሲፈጽሙ አጋራቸውን ትተው በፊልም ያዩትን እያሰቡና እያሰላሰሉ ይፈጽማሉ። ይህም በአእምሮ የሚፈጸም ዝሙት ነው።
- ባሎች/ሚስቶች ሆይ ይህን የሚያደርጉ ካሉ አቁሙ! ልትሏቸው ይገባል። ይህ ቅድስና የተለየው ሕይወት ከትዳራችን ሊወጣ ይገባል ካላላችሁ ከፍያለ እንቅፋት በፊታችሁ ይጠብቃችኋል።
- ሌላ ሰው እያሰቡ ለሚፈጸም ድርጊት መሣሪያ አንሆንም፣ ሰውነታችን  የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ለ Pornography አይደለም! ማለት ከኦርቶዶክሳውያን ተጋቢዎች ይጠበቃል።
- ካልሆነ ግን ይህ የዝሙት ዲያቢሎስ በትዳራችሁ ሆኖ ልጆቻችሁንም እንዲያጠቃ ትፈቅዱለታላችሁ።

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

## *የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች …*

- ልጆቻችሁም በሰይጣን አሠራር ለመወሰዳቸውም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ትሁናላችሁ።
- በPornography አመለካከቱ የተበላሸ ሰው በየትም ሥፍራ ባለው ግኑኝነት በሥጋ ፍትወት እጅግ የተቃጠለ ይሆናል። ቀልዱ፣ በሥራ ገበታው ከሚያገኛቸው ተቃራኒ ጾታዎች ጋር የሚኖረው አጋጣሚ ሁሉ በሥጋ ፍትወት እጅግ የተበረዘ ይሆናል።
- ዛሬ ማስታወቂያዎች ሁሉ በሥጋ ፍትወት እጅግ የተበረዙ ናቸው። ለምን? ሰው እየተሳበባቸው ስለሆነ፣ ሰው ወሲባዊ አእምሮ ይዞ የሚራመድ እየሆነ ስለመጣ ነው።
- ተራክቦ ሳያደርጉ መኖር እንደሚቻል እንመን። ሕይወታችን በሙሉ ግን የሥጋ ፍትወትን መፈጸም ከሆነ ያለርሱ መኖር ያቅተናል። ከዚህ ደረጃ የሚያደርሰንም ሰይጣን ነው።
- እግዚአብሔር ለትዳር ሁሉን አስተካክሎ ሠርቶታል። የሠራውም በፍጹም ቅዱስ ነው። ቤተ ክርስቲያን በተጋቢዎች መካከል የሚደረግን ግኑኝነት አስመልክቶ በፈጠረውና በፈቀደው መልክ ብቻ የሚፈጸመውን ታስተምራለች ትደግፋለች። ከዚያ ውጪ የሆነውን ግን ትቃወማለች።
- በቤተ ክርስቲያናችን በወንድም ሆነ በሴት በትክክለኛው የተራክቦ አካላቸው በኩል የማይፈጸም ግኑኝነት(አካለ ዘር ማደጉን መስፋቱን/መጥበቡን… ሳይቀር እየመረመሩ… አልፈው ወጥተው… የሚያደርጉትን ሁሉ) የእግዚአብሔር እቅድ እንዳልሆነ ታስተምራለች። በትዳር ያለ ግኑኝነት ደስታ የጋራ የሆነ ገጽታ ያለው ነውና።
- ከመሥመር በወጣ መንገድ የሚገኛኙ ወደ ማይወጡበት ከፍተኛ አደጋና ችግር ውስጥ ይወድቃሉ።

# <u>መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም</u>

***<u>የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች …</u>***

- ወደ አንዱ የአካላችን ክፍል የገባ ኃጢአት በቀላሉ አይወጣም፡፡ የናርኮቲክ ሱስ ያለባቸው ሰዎች የወሲብ ሱስ ካለባቸው እጅግ የተሻሉ ናቸው፤ ምክንያቱም ችግራቸው በቀላሉ ሊወገድ ይችላልና፡፡
- ጻድቁ ኢዮብ በሕይወቱ የወሰነው ከላይ የተጠቀሱትን አስመልክቶ የሚለን ትምህርት ሊሆነን ይገባል፡፡
- ‹‹ ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ

  እንግዲህስ ቈንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ? የእግዚአብሔር እድል ፈንታ ከላይ፥

  ሁሉንም የሚችል አምላክ ርስት ከአርያም ምንድር ነው? መዓትስ ለኃጢአተኛ፥

  መለየትስ ለሚበድሉ አይደለምችን? መንገዴን አያይምን?

  እርምጃዬንስ ሁሉ አይቈጥርምን? በእውነተኛ ሚዛን ልመዘን፥

  እግዚአብሔርም ቅንነቴን ይወቅ፡፡

  በሐሰት ሄጄ እንደ ሆነ

  እግሬም ለሽንገላ ቸኵላ እንደ ሆነ፥ እርምጃዬ ከመንገድ ፈቀቅ ብሎ፥

  ልቤም ዓይኔን ተከትሎ፥

  ነውርም ከእጄ ጋር ተጣብቆ እንደ ሆነ፥ እኔ ልዝራ፥ ሌላ ሰውም ይብላው

  የሚበቅለውም ሁሉ ይነቀል፡፡ ልቤ ወደ ሌላይቱ ሴት ጐምጅቶ እንደ ሆነ፥

  በባልንጀራዬም ደጅ አድብቼ እንደ ሆነ፥ ሚስቴ ለሌላ ሰው ትፍጭ፥

  ሌሎችም በእርስዋ ላይ ይጐንበሱ፡፡ ›› *<u>መጽ ኢዮ 31፡1-10፡፡</u>*

# መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

***የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች ...***

- ሌላው አደናቃፊ ምክንያት ባሎች አስቀድሞ የዘር ፍሬዬ ይፈሳል ሲሉ፣ ሚስቶች ደግሞ በግኑኙነቱ የተነሳ እታመማለሁ፣ እቆስላለሁ ፊስቱላ ይሆንብኛል ብሎ ማሰብና መፍራት ነው፡፡
- አንድንድ ዶክተሮችም ጠባብ ስለሆነ ዳይሌት መደረግ አለብሽ ብለው በአግባብ ወዳልተጠና ሴቶቹን ወደ ሚያስጨንቅ አቅጣጫ ይመራሉ፡፡
- የልጅን ጭንቅላት የሚያክል ነገር የሚያስወጣ አካል የባልን የዘር አካል ማሳለፍ ይሳነዋል? ተረጋግተን እንራመድ ፍርሃቱም ሆነ ሕመሙ ያኔ ይርቅልናልና፡፡
- በተጨማሪነት የምናነሳው አደናቃፊ ነገር ተራክቦን ለመፈጸም የሚያስችል ፍላጎት ማጣት ነው፡፡ በሥራ ጫና መብዛት የተነሳ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለተራክቦ ያላቸው ፍላጎት ተዛብቶባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ለመጥቀስ ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ አገር የተደረገ ጥናት እንደጠቆመው 43% ክርስቲያኖች ሴቶችና 31% ያህል ክርስቲያኖች ወንዶች ከሥራ ጫና መብዛት የተነሳ ለተራክቦ ያላቸውን ፍላጎት አጥተው ተገኝተዋል፡፡

# የተቀደሰውን ጋብቻ የግኑኙነት ቅድስና የሚያጠናክሩ ምክንያቶች

1. ጸሎት፡፡

2. እርስ በርስ መግባባት ወይም መነጋገር

3. እገዛ ሲያስፈልገን እንዲደረግልን መጠየቅ

4. ምቹ ጊዜና ቦታን መምረጥ

5. ፈቃዳችንን ለመፈጸም ያለብንን ስንፈት በየጊዜው እያከሙ ማሻሻል፡፡ ለምሳሌ ስንፈት ያለባቸው አለብን ብለው ራሳቸውን ሳያሳምኑ በየጊዜው ከትዳር አጋራቸው ጋር በግልጽ እየተነጋገሩ ክፍተቶቻቸውን ማጥበብና የችግራቸውንም መፍትሔ በጋራ ፈልገው ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡

6. በመካከል መቀዛቀዝ ካለ በዚህ ችግራችን ዙሪያ ምክር በማግኘት ማስተካከል

7. በትዳሩና በግኑኙነቱ ፍቅር እንዲሰለጥን በእግዚአብሔር ግብ መመራት፡፡ እነርሱም አንድነትን መጠበቅ፣ በተሰጠን የትዳር ስጦታ ማመስገንና በትዳሩ ደስታን ማግኘት ናቸው፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

... ክፍል ስምንት ይቀጥላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።